# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና

# ትንበያ መጽሔት

## ከዲሴምበር 11-20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከዲሴምበር 21-31 እና ከጃንዋሪ 1-10/ 2025

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ዲሴምበር 2024

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ - 1 -
ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 2 -
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 3 -
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 3 -
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 3 -
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 4 -
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 4 -
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 5 -
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31 /2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 5 -
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 21-31, 2024 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ - 6 -
ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 21-31, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 6 -
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 6 -
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 6 -
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 7 -



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

በዲሴምበር የሁለተኛዉ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ተስተውሎባቸዋል፡፡ በተለይም የሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛው፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ነበራቸው። በሌላ በኩል ወደ ሀገራችን ሲገባ ከነበረዉ እርጥበት አዘል አየር ከተፈጠረዉ የዳመና ሽፋን ጋር ተያይዞ በመጨረሻዎቹ ቀናቶች የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ላይ ከአብዛኛው አከባቢዎች ላይ ቀንሶ ተስተዉሏል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም በአዲግራት 2፣4.6፣ 4፤ በአይደር 4.2፤ በሐሮማያ 2.0፣ 1.2፣ 2.6፣ 1.8፣ 1.4፣ 1.0፣ 1.6፣ 1.2፣ 0.2 ፤ በአለም ከተማ 4.8፣ 4.8፣ 3.8፣ 4.0፣ 3.2፣ 4.0፣ 4.8፤ በአምባማሪያም 3.6፣ 4.0፣ 3.2፤ 4.0፣ 4.2፣ 3.5፣ 4.0፣ 4.2፣ 3.5፣ 4.0፣ 4.2፣ 3.5፣ 4.0፣ 4.2፣ 4.5፣ 4.8፤ በአርሲ ሮቤ 3.5፣ 3.0፣ 2.0፣ 3.0፣ 3.5፣ 3.5፣ 3.5፣ 2.5፣ 4.5፤ በባቲ 4.4፣ 4.8፣ 4.6፤ በቡኢ 2.6፣ 2.0 2.0፣ 3.0፣ 2.4፣ 2.2፣ 2.0፣ 2.6፣ 2.8፣ 4.0፤ በኮምቦልቻ 4.6፤ በደብረብርሀን 2.4፣ -0.4፣ 0.2፣ -2.6፣ 2.2፣ 1.8፣ 0.8፣ 2.0፣ 3.4፣ 4.4፤ በዳንግላ 4.8፣ 4.6፣ 4.2፣ 4.0፤ በደባርቅ 4.5፣ 4.5፤ ደብረ ወርቅ 4.8 ፣ በቢሾፍቱ 3.0፣ 1.0፣ 1.2፣ 2.4፣ 2.5፣ 2.0፣ 2.0፤ በእነዋሪ 4.2፣ 3.5፣ 3.5፣ 2.5፣ 4.5፣ 4.5 ፤ በፊቼ4፤ በእምድብር 4.6፤ በጅግጅጋ 4.0፣ 4.2፣ 2.0፣ 2.2፣ 1.4፣ 4.0 4.6፣ 0.2፣ 0.0፤ በማይጨዉ 4.8፣ 3.0፤ 4.8፤ በመሐል ሜዳ 3.6፣ 3.2፣ 0.2፣ 1.0፣ 4.2፣ 4.5፣ 4.0፣ 2.5፣ 3.8፣ 4.0፤ በሞጣ 4.4 ፤በሮቤ 4.4፤ 4.8፣ 4.8፣ 4.8፤ በሾላ ገቢያ 4.0፣ 4.0፣ 3.0፣ 1.2፤ 3.0፣ 3.0፣ 2.1፣ 2.0፤ በወገል ጤና 2.2፣ 3.8፣ 2.6፣ 1.8፣ 0.2፣ 3.0፣ 4.4፣ 3.5፣ 3.5፤ እንዲሁም በወረይሉ 4.8 በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1)፡፡

በሌላ በኩል በጥቂት የምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጨረሻዎቹ አራት ቀናት ሳሳ ያለ የደመና ሽፋን የነበራቸዉ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያዞ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በጅንካ 1.1፣ በአርባምንጭ 1፣ በጋምቤላ 0.2 ፤ እንዲሁም በሳዉላ 0.1 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በጅንካ፣ በአርባምንጭ፣ በጋምቤላ፤ እንዲሁም በሳዉላ ላይ እስከ 1.1 ሚሜ የሚደርስ ከ1-2 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ እንዲሁም አብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍል በደረቃማው የአየር ሁኔታ ስር ቆይተዋል፡፡ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በሁሉም የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በተለይም በመጀመሪያዎቹ አጋማሽ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለ እንደነበር የተተነተኑ የእርሻ ሚትዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ። ይህም ሁኔታ መኸር አብቃይ በሆኑት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመካሄድ ላይ ላለው ሰብል ስብሰባ እና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር (ካርታ 4)፡፡።





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች ከነበረው ደረቅ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ በአፈር ውስጥ የነበረው እርጥበት ደረቃማ እንደነበረ የተተነተኑ የውኃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 5)፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31 /2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ጸሀያማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በፀሀይ ኃይል ታግዘው ከሚፈጠሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የደመና ሽፍን ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገራችን አከባቢዎች ማለትም የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ክፍል፣ የጉጂና የቦረና ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ( ካርታ 7 )፡፡ በሌላ በኩል በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየታየ ያለው የበጋው ደረቅና ፀያማ የአየር ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱ እና የማለዳው ቅዝቃዜ በአንፃሩ እንደሚቀንስ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6 )፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 21-31, 2024 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከዲሴምበር 21-31, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመጪዎቹ የጃንዋሪ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየታየ ያለው የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ በአንጻሩ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱ እና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚቀንስ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገራችን ሶማሌ ክልል ደቡባዊ ክፍል፣ የጉጂ የቦረና ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገራችን ክፍሎች ላይ የሚኖረው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ የመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በመሆኑም አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት ሰብልን ከማሳ የማንሳትና



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

የማከማቸት እንዲሁም የመውቃት ተግባራትን በማከናወን ምርትን ከብክነት መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል በምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ክፍል፤ የጉጂና የቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች አካባቢዎች የሚኖረው እርጥበት በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበጋ ወቅት ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችም ሆነ ለእንስሳት የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩል ከሚኖረው የዳመና ሽፋንና የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ከፍተኛ ቦታዎችን ጨምሮ ተስተውሎ ነበረው የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ ቀስ በቀስ ከመቀነሱ ጋር ተያይዞ በበጋ ሰብሎችና በእንስሳት ላይ የነበረው መጠነኛ ጉዳትም እንደሚቀንስ ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 30/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት አብዛኛዎቹ የሀገራችን ተፋሰሶች ላይ ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር የሚቆይ ቢሆንም በጥቂት የሀገራችን ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡ በተለይም የታችኛውና የመካከለኛው ኦሞ ገቤ፣ ጥቂት የላይኛው ባሮ አኮቦና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ መጠናኛ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡

በሌላ በኩል በአብዛኛው አዋሽ፣ ተከዜ፣ አፋር ደናክል፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ መረብጋሽ፣ አይሻ፣ አባይ እንዲሁም ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ደረቅ የአየር ሁኔታ ስር ይቆያሉ፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et